የምፅዓቱ የምሥራች

ቅጽ 77 ቁጥር 6(918)
እና
ቅጽ 77 ቁጥር 718 (919-920)

“ቃልህ ሕያው አድርጎኛልና...” (መዝሙረ ዳዊት 118:50)

የእግዚአብሔር ቃል መንፈሳዊ ህይወት ይሰጣል

(በስፓርጆን እና በኮንሎን)

መንፈሳዊ ሰዎች በየቀኑ ይታደሳሉ። በእግዚአብሔር ከመተማመን ለአፍታም ወደኋላ አይሉም። የሚያነቃቃውና ጸጋ የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው። በእግዚአብሔር ቃል የዳነ ፍጥረት በእግዚአብሔር ቃል ይቀደሳል። የመንፈሳዊ ሰዎች ብቃት የሚለካው ከእግዚአብሔር ጋር ባለቸው ቁርኝት መጠን ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሰዎች ዘላለማዊነት የሚያገኙበት መንገድ ነው። *“በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ እውነት ነው”* (ዮሐንስ 17:17)፣ *“በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ”* (ዮሐንስ 8:31)

የእግዚአብሔር ቃል የመነቃቃት መሪ (መስታወት) ነው።

“ቃሉን የሚሰማ የሚያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስታወት የሚያይን ሰው ይመስላል፤ ራሱን አይቶ ይሄዳልና ወዲያውም እንደምን እንደሆነ ይረሳል። ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍፁሙን ሕግ ተመልክቶ የሚዐናበት ሥራንም የሚሰራ እንጂ ሰምቶ ሚረሳ ያልሆነው በሥራው የተባረከ ይሆናል።”
(ያዕቆብ 1:23-25)

መስታወት የሚመለከተውን ሰው ገጽታ ያሳያል መጽሐፍ ቅዱስም እንዲሁ ያሳያል። ማንም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን በማስተዋል ባጠና ቁጥር ማንነቱን በሚገባ ያውቃል የንጉስ አካን መጎምጀት፣ የንጉስ ዳዊት መውደቅ፣ የኤልያስ መሸሸግ፣ የያዕቆብ አታላይነት፣ የሀናንያና የሰጲራ ሀሰተኝነት፣ የጴጥሮስ ክህደት፣ የጳውሎስና የሲላስ መገረፍና እስከመጨረሻው መጽናትና፣ የጳውሎስ መከራና ልዩ ጥበቃ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይታያሉ፤ ይነበባሉ።

ከዚህ በላይ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለ ክብርና ግርማ ይተነተናል። *“ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መገበገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን”* (2 ቆሮንቶስ 4:6)

የእግዚአብሔር ቃል ህይወትን የሚያጸዳ የሚያድስ ኃይል አለው። *“ክርስቶስ ዳግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ በውሃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን*

አንጽቶ አሳልፎ ሰጠ” (ኤፌሶን 5:25)

“እናንተ ንጹህ ናችሁ” (ዮሐንስ 15:3)

“ጎልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል? ቃልህን በመጠበቅ ነው” (መዝሙር 118:9)

በዚህ ዓለም ኑሯችን እኛ ክርስቲያኖች መመንገደኛ ከዓለም ክፉት በየቀኑ ከሚከበን በመሸሸና በመለየት ነው። ከዓለም ከሰይጣንና ከስጋ እርኩሰት እራሳችንን የምናጠራው ሌሎቹም እንዲጠሩ የምንመክረው በቃሉ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል የነፍስ ምግብ ሲሆን ስጋችንም ተቀድሶ የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመሆን የሚችለው በቅዱስ ቃሉ ነው። (1ኛ ጴጥሮስ 2:2)

አማኞች በእምነት እያደጉ ሲሄዱ ጠንከር ያለ የነፍስ ምግብ(ቃል) መመገብ አለባቸው። ብዙዎች የሚሳሳቱበትን ከእውነት መንገድ የሚወጡበትን ሁኔታ ማስቆም የሚችል

የምዕአቱ የምስራች ወንጌል አገልግሎት
ዋና አሳታሚ፡ ሬክ ካርማይክል
የአማርኛው ተርጓሚ፡- ሕዳፍርስ(ሕዲ) ሀብቴ
ተጠሪ፡- አልማዝ አሳየ

ዮፓ.ሣ.ቁ 8986
አዲስ አበባ/ኢትዮጵያ

የእግዚአብሔር ቃልና ቅዱስ መንፈሱ ብቻ ስለሆነ ጠንክር ያሉ ትምህርቶችና ምክሮችን ከእግዚአብሔር ቃል በመውሰድ በራሳችንም ሆነ ዲሲፕሊኖቻችን ጥገኞች እንዳይሆኑ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በማነፃፀር ልናጠና ብቻ ያስፈልገናል። ማደግ የማይፈልጉ ክርስቲያኖች ሁልጊዜ ቀለል ያለውን የእግዚአብሔር ቃል ማጥናት ሲፈልጉ ብርቱ መሆን የሚፈልጉ ግን ሁሉንም የእግዚአብሔር ቃል ጠጣር ወይም ከባድ የሆነውን ጭምር ሊያጠኑ ይወዳሉ። *"ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በስራቸው የለመደ ልቦና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው"* (ዕብራውያን 5:14)

የእግዚአብሔርን ቃል አዘውትሮ የሚመገብ ሰው መንፈሳዊ ጥንካሬው ይጨምራል።

ከእግዚአብሔር ቃል የሚርቀው ግን በመንፈሳዊ ድካም ይሞላል። ለውድቀትና ሌሎቹን ለማሳሳትም ምክንያት ይሆናል።

ሰዎች በስጋዊ ምግብ ወፍረው መንፈሳቸው የከሳ ኃጢያትን የማይፀየፉ ነውርን እንደደስታ የሚቆጥሩ ቤተክርስቲያን ተብሎ በሚጠራው ሳይቀር በብዛት በማየት ላይ ስለሆንን ከዚህ እርም ራሳችንን ሌሎችንም እንጠብቅ።

ብዙ የፀኑ ክርስቲያኖች ባለፈው ዘመንም ሆነ ባለንበት ዘመን የሰይጣንን፣ የዓለምንና የስጋን ፈተና የሚያሸንፉት በቃሉና በጸሎት በመትጋት ነው። ቃሉ በጥልቀት የሌላቸው ለልዩ ልዩ መንፈሳዊ ውድቀቶች ለሀሰት ትምህርቶችና ይባስ ብሎም ወደ ድፍረት ኃጢያት ይገባሉ።

ሐዋሪያቱ የሚሰብኩትና የሚያስተምሩት በሰው ጥበብና ፍልስፍና በመሞላት ሳይሆን ቅዱስ መንፈሱን በሚልከው በእግዚአብሔር ቃል በማጥናት ነው። "ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበር እንጂ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም።" (1ኛ ቆሮንቶስ 2:4)

የእግዚአብሔር ቃል መሪ ብርሃን ነው

ሰይጣን በክርስቲያኖች ዙሪያ ዘወትር የሚፈጥረውን ፈተና ቅዱሳት መጻህፍትን የሚያጠኑ የሞላባቸው ሰዎች በእግዚአብሔር ብርሃን ስለሚሞሉ ክፋትን በመለየት ራሳቸውንና ሌሎችን ከጥፋት ይመልሳሉ። *"ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው"* (መዝሙረ ዳዊት 118:5)፤ *"ኃጢአተኞች ወጥመድ ዘረጉብኝ ከትእዛዝህ ግን አልሳትሁም"* (መዝሙረ ዳዊት 118:110) ቀናው የእግዚአብሔር መንገድ ሁልጊዜ በቀላሉ የሚገኝ አይሆንም። እውነት ብዙ ጊዜ ሀሰት የከበባት በብርቱ ትግልና መከራ የምትጣበቅ ናት። የእግዚአብሔር ቃል ሰዎች በበጎ በመልካም ኑሮ መኖር እንዲችሉ የሚመክር የሚመራ የሚያስተካክል መሳሪያ ነው።

"የእግዚአብሔር ሰው ፍፁምና ለበጎ ስራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳፅ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል" (2 ጢሞቴዎስ 3:16)

የእግዚአብሔር ቃል ሁለት አቅጣጫ ስለት ያለው ተናጋሪውንም ሰሚውንም ስለሚያስተካክል ነው። (ዕብራውያን 4:12) መንፈሳዊ ሕይወት የሚገኘው በእግዚአብሔር ቃል በመመራት ነው። (መዝሙረ ዳዊት 118:1-3) የእግዚአብሔር ቃል የሰይጣንን ክፉ ስራዎች ለማፍረስ መሳሪያ ነው (ኤፌሶን 6:17) ጠንካራ ብረቶች በተለይ ወርቅ የሚጠራው በእሳት የመሆኑን ያህል የእግዚአብሔር ቃል የአማኞችን ህይወት እንደ እሳት ያጠራል። (ኤርሚያስ 20:9) እንደ አለት ወይም እንደ ድንጋይ የጠጠረ የሰውን ክፉ ልብ የእግዚአብሔር ቃል ይሰብራል። (ኤርሚያስ 23:29)

ከሁሉ በላይ እግዚአብሔር ቃል ለትክክለኛው በረከትና ብልፅግና መሰረት ነው፤ ዘር ነው። (ሉቃስ 8:11) ስለዚህ ክርስቶስን በመምሰል ለመኖር ቅዱስ ቃሉን እንነርበት። (ዮሐንስ ወንጌል 15:7)

የምጽአቱ የምስራች ሁሉንም የክርስቶስ ማህበሮች የሚያገለግል ነው::

የምጽአቱ የምስራች ዋናው የእንግሊዘኛ እትምም ሆነ ሌሎች የትርጉም ስራዎች ሁሉ ከአንድ ቡድን ወይም ማህበር ጋር ያልተቆራኘ ሁሉንም የክርስቶስ ማህበሮችና አካላት ለማገልገል የተቋቋመ የወንጌል ማህበር የሥነፅሁፍ አገልግሎት ነው::

በክርስቶስ ቃል መሰረት እያንዳንዱ ክርስቲያን ሌላውን መውደድ እንዳለበት የተናገረውን በተግባር ለመተርጎም ይጥራል:: "እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀመዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ" (ዮሐንስ 13:35)

የምጽአቱ የምስራች የወንጌል መነቃቃት አገልግሎት የተመሰረተው በቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ላይ ነው:: ጌታ ኢየሱስ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ አንድ አምላክ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የሆነ በክርስቶስ ያመኑት ሁሉ በትንሳኤ የመንግስቱ ተካፋዮች መሆናቸውን የሚቀበል አገልግሎት ነው:: (ኢሳያስ 7:14) የምጽአቱ የምስራች የጌታን ዳግም ምጽአት ሰዎች በቅድስና እንዲጠበቁና ሌሎቹን በወንጌል የሚደርስ በዘላለም ሕይወት የሚያምን ህብረት ነው::

በመጨረሻው ዘመን በእግዚአብሔር ቃል ጥሞና ያስፈልጋል

ሐዋርያው ጳውሎስ ለወጣቱ ጢሞቴዎስ በዳፈለት ሁለተኛው መልዕክቱ በመጨረሻ ዘመን በተባለው የሚታዩትን ክፉ ነገሮች በማስገንዘብ አማኞች በቅዱስ ቃሉ በጥሞና ራሳቸውን በማዘጋጀት በቅድስና እንዲጠብቁ መልዕክቱን ልኮልናል:: (2 ጢሞቴዎስ 3:1-5)

እነዚህ የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች ምን ያህል በአካባቢያችን በዓለም ዙሪያና በሀገራችን ኢትዮጵያ በመታየት ላይ መሆናቸውን ህሊና ያለው ሁሉ የሚረዳው ነገር ነው:: ራስን መውደድ፣ ገንዘብ መወደድ፣ የቅድስና መጥፋት፣ ለወላጆች ያለመታዘዝ፣ ትዕቢት፣ ተሳዳቢነት፣ ሐሜተኝነት፣ ችኩልነት፣ የእግዚአብሔርን ኃይል መካድና የመሳሰሉት በይፋ ይታያሉ:: ስለዚህ እነዚህን ክፉ ስራዎች ለመሸሸና ሌሎችንም ለማስመለጥ የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ በቅዱስ ቃሉ በእርጋታ ጥሞና ሊያደርጉ በጣም ያስፈልጋል::

ይህን ምክር ሰምተን ዛሬውኑ በጌታ ቅዱስ ቃል ህይወታችንን በጥሞና ጸሎት እንምራው::

ሪክ ካርማይክል - አሳታሚ

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ሲጎበኝት

በብዙ ዘመናት በጥላቻ በረሀብና በእርስ በርስ ጦርነት በተቀደሰው የእግዚአብሔር ቤት ሳይቀር ለነገሰባት ሃገራችን-ኢትዮጵያ ፍጹም ካልተጠበቀ ስፍራ ባልተጠበቀ ጊዜ እግዚአብሔር ሰው ማስነሳቱን የእግዚአብሔር መንፈስ ያለው ሁሉ ይረዳዋል::

የቀድሞ ነገስታት በፉክክር አንዱ ሌላውን በማሳደድ በመግደል ቀሳውስቱ ፓስተሮቹ ኢማሞቹ ሁሉም በመከፋፈል ክፉ ሆነው ለትውልድ ክፋትን ያስተላለፈች በቅዱስ መጽሐፉ ግን በብዙ የተጠቀሰች ሀገራችን ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በፍቅር ልብ የይቅርታ ልብ የምህረት ልብ ያለው መሪ ያገኘችው በዚህ ዘመን ነው:: ቅዱስ ቃሉ *"የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ በስጋ ለባሽ የሚታመን የተረገመ ነው"* የሚለው እንደተጠበቀ ሆኖ *"እንደ ልቤ"* ያለው የእግዚአብሔር መሳሪያ ሰው የሆነው ንጉስ ዳዊት እንደሆነ ቅዱስ ቃሉ ይመሰክራል::

ዶክተር አብይ አህመድ አሊ ገና ሥልጣኑን ሳይዝ ቃል ኃይል ያለው ነው ብሎ የተናገረው በዮሐንስ ወንጌል መጀመሪያ ላይ የተገለጸው ቃልም ህይወትም አምላክም የሆነው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በሀገራችን ኢትዮጵያ ይህን የመሰለ የተባረከ ሰው የነበረው ከ1000 ዓመታት በፊት በህዝቡ

"ፍቅረ ቅዱስ" ሚል ስያሜ የተሰጠው ደግ የዋህ ንጉስ ዮሐንስ የሚባለው በእንግሊዘኛም ብዙ የተዘገበለት ንጉስም ካህንም የሚሉት ንጉስ "ፕሬስተር ዮሐንስ" ወዲህ ሀገራች ያገኘችው ደግ መሪ የፍቅር መሪ ዶ/ር አብይ አህመድ ነው።

የደግ መሪ መሰረቱ የእግዚአብሔር ቃል ለመሆኑ ታሪክ ይመሰክራል። በሀገራችንም ይህ በሕዝቦቹ እጅግ የተወደደው ጠቅላይ ሚኒስትር ቃሉን የሚወድ የሚያነብ ነውና እኛም ዜጎቹ በተለይ ክርስቲያኖቹ የበጎነት ሁሉ ምንጭ የሆነውን የሰላምና የፍቅር መገኛ ያለበትን ቅዱስ ቃሉን በትጋት እናንብበው። በህይወታችንም ተግባራዊ እናድርገው። በዚህ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ኢትዮጵያን ይጎበኛል፤ ይባርካታል።

አደፍርስ(ኤዲ) ሀብቱ

የምጽአቱ የምስራች አስተባባሪ

መንፈሳዊ መታደስ(መነቃቃት) እና ቅድስና በቃሉ ነው

መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች መጻሐፍት የሚለይበት መጠሪያው ቅዱስ በሚል መለያ መገለፁ ነው። ይህ የቅድስና መጽሐፍ ሰዎችን የፈጠረ ዳግም የወለደና የሚለውጥ በመጨረሻም ከሞት የሚያስነሳ ቅዱስ መንፈሱ ያለበት መጽሐፍ ነው።

ዶክተር መ.ዲ የተባለው ሰባኪ እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ከኃጢያት ያርቀናል ወይም ኃጢያት ከመጽሐፍ ቅዱስ ይለየናልና ዛሬውኑ አንዱን እንምረጥ። (መዝሙረ ዳዊት 118:11)

ንጉስ ዳዊት በመዝሙሩ 118 ቁጥር 25 ላይ እንዳለው እንደቃሉ ህያው እንዲያደርገን በቃሉ በመሞላት ዘወትር ልንገኝ ይገባናል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከል የሆነው ክርስቶስ ራሱ ቃል ሲሆን ይህ ቃል በመጀመሪያ የነበረ ከዚያም ስጋን የለበሰና አብሮን ያለ ወይም አማኑኤል የሆነው እግዚአብሔር ነው። (ዮሐንስ 1:1-14) የክርስቶስ መንፈስና ማንነት በእኛ የሚሰርጸው ለሌሎችም የሚተርፈው ቃል የሆነ ክርስቶስን ከቅዱስ ቃሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ በጥሞናና በማስተዋል ስንሞላ ነው። (2 ቆሮንቶስ 4:11 ፣ ቆላሲያስ 2:9)

የመጽሐፍ ቅዱስ ታምራቶች መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ሰው ዘር ከመላኩ ጊዜ ጀምሮ በታምራት የተሞላና ተዓምረኛውን ፈጣሪ የሚገልጽና የሚያስተዋውቅ ቅዱስ መጽሐፍ ነው። ሰዎች አያሌ ልዩ ልዩ መጽሐፍት ሊያነቡ ወይም ሊተረጉሙ ቢችሉም ዓመቱን በሙሉ በየቀኑ በየወሩ በየደቂቃውና ሰከንዱ የሰዎችን ልብ በሚመስጥ መልኩ ኃይል ያለው የሚለውጥ መጽሐፍ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ በአለም ዙሪያ አልተገኘም፤ አይገኝም።

የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ ክፍሎች አንድ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን እጅግ በተራራቁ ዘመናትና ስፍራዎች በተለያዩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተፃፉ የብዙ መጽሐፍት ስብስብ ነው።፤

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሀፊዎች ስፍራና ማንነት ሀገር ቢለያያቸውም ዋና መልዕክታቸው ግን እርስ በርሱ የሚስማማ ማዕከላዊ ሃሳቡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። (ዮሐንስ 5:39)

የመጽሐፍ ቅዱስ ተዓምረኛነት ራሱ ቃል በሆነው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተከናወኑ ድንቅ ተዓምራቶችና የእርሱ ተከታዮችም የበለጠ ያደርጋሉ በተባለለት የተሰፋ ቃል መሰረት ነው። (ዮሐንስ 14:12)

ቅዱስ ቃሉና የጸሎት አገልግሎት

(በእንድሪው ሙሬ)

"በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችኋል" (ዮሐንስ 15:7) በጸሎት ህይወታችን እግዚአብሔር ምልጃችንን ሰምቶ የምንጠይቀውን የሚሰጠን በቅዱስ ቀሉ ይህንን ተስፋ ስለሰጠን ነው።

እግዚአብሔር ያዘዘውን፤ ታማኝ ፈጽመዋል። እግዚአብሔር እራሱን ለሰው ዘር መዳን የሰጠ በመሆኑ በትክክል የሰው ዘር የሚያስፈልገውን ሲጠይቀው የሚሰጥ አምላክና ጌታ ነው። የክርስቶስ ቃሎች ሁሉ የእግዚአብሔር ቃሎች ናቸው፤ ኃይልና ሥልጣን አለባቸው። *"የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው፤ ሕይወትም ነው።"* (ዮሐንስ 6:63) ዲዳና የማይሰማ ጆሮ ያላቸውን የከፈተና የሚከፍት፣ ተናግረው የማያውቁትን እንዲናገሩ ያስቻለና የሚችል፣ ሕያው የእግዚአብሔር ቃል ነው።

የእግዚአብሔርን ቃል በጆሯችን ሰምተን በልባችን ስንጠብቅ ለሌሎች በረከቱን በቃላችን ማስተላለፍ፣ መመስከርና መስበክ እንችላለን። ለፈጣሪና ለሰዎች መናገር፣ መዘመር፣ መስበክ የምንችለው የተባረከ አንደበትና ሰሚ ጆሮ ሲኖረን ብቻ ነው። *"ጌታ እግዚአብሔር የተማሩትን ምላስ ሰጥቶኛል"* (ኢሳያስ 50:4) ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት የሚኖረን በቅዱስ ቃሉ ነው።

የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት የእግዚአብሔርን ቃል ከማንበብ ይለያል። የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ ትንሽ ህብረት ሲኖረን በቅዱስ መንፈሱ በመመራት የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ግን ሕያው የሆነው እግዚአብሔርን በተጨባጭ ማግኘት ነው። ይህን የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማት በፍጹም መታዘዝን ይጠይቃል።

ይህንን ባለመታዘዝ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ልናጣ እንችላለን። የሰው አስተሳሰብ ከእግዚአብሔር አስተሳሰብ ስለሚለይ በእግዚአብሔር ቃል በመመራት የእግዚአብሔርን አስተሳሰብ እናግኝ። *"ሀሳቤ እንደ ሀሳባችሁ መንገዳችሁም እንደመንገዴ አይደለምና ይላል እግዚአብሔር ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ ሀሳቤም ከሀሳባችሁ ከፍ ያለ ነው። ዝናብና በረዶ ከሰማይ እንደሚወርድ ምድርንም እንደሚያረካት ታብቅልና ታፈራም ለዘሪ ንቃውያለማሰብያ ዝነደማሰብያ እንሚዘክ ሰማይ እንደማይመለስ ከአፌ የሚወጣ ቃል እንዲሁ ይሆናል።"* (ኢሳያስ 55:8)

ይህ የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኛ መጥቶ ብንሰማው የሚፈጽመውን ይመሰክራል። *"እግዚአብሔር እንደተናገረው አብርሃም ተለየ"።* (ዘፍጥረት 12:4) የአብርሃም ሕይወት ከስጋ ዘመዶቹ በመለየት ከእግዚአብሔር ጋር ተቆራኘ። ከዚያ በኋላ የሚናገረውም ሆነ የሚያደርገውና የሚሄድበት ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ቃሎቹ በእናንተ ቢኖሩ በማለት በአዲስ ኪዳን የሚነግረን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ህይወታችን በማዛመድ የእግዚአብሔር ሀሳብ በእኛ ሲከናወን የሚታየውን ውጤት ለማሳየት ነው።

በእግዚአብሔር ቃል በመኖር እግዚአብሔርን ስንታዘዝ የሚኖረን ህይወት የእግዚአብሔር ስራዎችና ፍሬዎች የሚታዩበት ይሆናል።

የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማና የሚኖርበት ሰው የእግዚአብሔር መሳሪያ ነው። የእግዚአብሔር መሳሪያ ማለት እግዚአብሔርን የሚያሳይ የእግዚአብሔር ፍቅር ምህረት ፈውስና በረከት የሞለው ነው። ሰዎች ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ ምንም ህይወት የሚሰጥ የሚያበረታ ተስፋን የሚሞላ ቃላት አያገኙም። የእግዚአብሔር ቃል ግን እራሱ ቃል የሆነው አምላክ ክርስቶስን ማግኘትና መቀበል ይሆናል።

የተባረከው ጌታችን ልጆቹ የሚያደርገን በቅዱስ ቃሉ በተሟላ ቅዱስ ጥምቀት በመቀበላችን ያንንም በቅዱስ ቃሉ በእምነት ስንጠብቅ ነው። (ማቴዎስ 28:19) (ኤፌሶን 2:8)

የእግዚአብሔርን ቃል ከኑሮው ጋር ያዋሀደ ሰው ሰላም የበዛለት በፈተናና በችግር በቶሎ ተስፋ የማይቆረጥ ከሁሉም በላይ ዘላለም የሚያኖረውን አዲስ ልደት ያገኘ ነው።

"እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው። ቃሉ ቀርቦልሃል ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው። ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሳው በልብህ ብታምን ትድናለህ። ሰው በልቡ አምኖ ይጸናልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።

መጽሐፍ በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርምና ይላል።"(ሮሜ 10:11-18)

ጌታ ሆይ ካልተገረዘ ክፉ ጆሮ አድነኝ የተቀደሰ ቃልህን ብቻ የሚሰማና የሚቀበል ጆሮና ልብን ስጠኝ! አሜን።

"ሳሩ ይደርቃ አበባውም ይረግፋል። በእውነት ሕዝቡ ሳር ነው የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ፀንታ ትኖራለች።" (ኢሳያስ 40:8)

የክርስትና ሰባኪዎችና አስተማሪዎች መሪ ቅዱስ ቃሉ ነው

በዚህ ምድር ላይ ስንኖር ለዘላለም የሚኖረውን ሰዎችን ከሰይጣን ከዓለምና ከስጋ እስራት ነጻ የሚያወጣውን ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ከማስተማር የበለጠ ትልቅ እድል የለም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ (ተከታዮቹ) ከማረጉ (ወደሰማይ ከመውጣቱ) በፊት ይህንን በሚገባ ያስተማረበት ክፍል በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ላይ ይገኛል።

ቅዱስ ቃሉና መንፈስ ቅዱስ ታላቅ አስተማሪያችን ነው ይህም በማይለወጥ ቅዱስ ቃሉ ተጽፏል። (ዮሐንስ 14:26) በክርስትናችን ገና ከመጀመሪያው ስለኃጢያት በመወቀስ ከዓምና ከሰይጣን ባርነት ነጻ እንድንወጣ የሚመራን መንፈስ ቅዱስ ነው። *"እርሱም መጥቶ ስለኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለፍርድም ዓለምን ይወቅሳል።"* (ዮሐንስ 16:8) ጌታ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ስለኃጢአት የሚወቅሰውና የእግዚአብሔርን ጽድቅ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘውን የሚገልጽልን በቅዱስ ቃሉ አማካኝነት ነው። *"በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም፣ ስጋ በሆነ በልብ ፅላት እንጂ በድንጋይ ላይ ያልተጻፈ"* 2ኛ ቆሮንቶስ 3:3)

የእግዚአብሔርን ቃል ሰዎች ካልሰሙ በዓለምና በሰይጣን ቆሻሻ ዓይናቸው የተጋረደና ጆሯቸው የተደፈነ ይሆናል። ነገር ግን ቅዱስ ቃሉን በመንፈስ ቅዱስ ኃይልን ስንገልጽላቸው ዓይናቸው ይበራናል፤ ጆሯቸውም ይከፈታል። ሕያው ቃሉን በመስማት ህይወትና ብርሃን ያገኛሉ። *"ወደ ጌታ (ክርስቶስ) ዘወር ባሉ ጊዜ መጋረጃው ይወሰዳል"* (2ኛ ቆሮንቶስ 3:17) ለራሳችን ጉዳይም ሆነ ለሌሎች በምንጸልይበት ጊዜ ቅዱስ ቃሉን ስንጠቀም መንፈስ ቅዱስ ራሱ እንዴትና ለምን እንደምንጸልይ ይገልጽልናል፤ ይመራናል። (ሮሜ 8:26)

ከጥንቷ ቤተክርስቲያን ጀምሮ በቤተክርስቲያን ታሪክ ሁሉ ቅዱስ ቃሉ በመንፈስ ቅዱስ መረዳትና ኃይል እየተሰበከ ብዙዎች ከሰይጣን ባርነት ተፈተው ነጻ በመሆን የጌታን ታላቅነት ለዓለም ሁሉ የሚመሰክሩ ኃያላን ይሆናሉ። *"ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርስም"* ያለው ከቃሉ ጋር በተዋሃደ ውኃ በመጠመቅና ያንን በእምነት በመጠበቅ የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ልጅነት ያሳያል። (ዮሐንስ 3:5 ፤ 16:14)

እጅግ በጣም የሚያስፈልገን ቅዱስ መንፈሱ ነው።

(በዌስሌ ዱዌል)

"በመንፈስ ተሞሉ" (ኤፌሶን 5:10) ከዚህ ዓለም ኑሮ ክርስቲያኖች ያለ መንፈስ ቅዱስ ምሪትና ጥበቃ መኖር እጅግ አደገኛ መሆኑን መረዳት አለብን። ለእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ለመኖር መንፈስ ቅዱስ ያስፈልገናል።

አደጋው የሚከተለው ባለፈው ህይወታች ጌታ በሰራልን ድንቅ ነገሮች ተመክተንና ተማምነን የጌታን ድጋፍ የቅዱስ መንፈሱን ምሪት ችል ስንል ነው።

አሁንም አሁንም ደጋግመን ማወቅ ያለብን መንፈስ ቅዱስ ሁሌም እንደሚያስፈልገን ማመን ነው። በዚህ በምጽአቱ ምስራች

የእንግሊዘኛውም ሆነ በትርጉም ስራ ያለ እግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነት የመጀመሪያዎቹ አሳታሚዎችና እኛም ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የምንተረጉም ተባባሪዎች ለዛሬው ቀን አንደርስም።

የድል ነሽ ሕይወትን በክፉ ሰይጣን፣ በአታላይዋ ዓለምና በደካማ ስጋችን ላይ ለመቀዳጀት የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ አነሳሽነትና ድጋፍ ያሻናል።

ውጤታማ ሆነው በዓለም ዙሪያ ታላላቅ ለውጦችን ያስከተሉት መንፈሳዊ መነቃቃቶች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ጀማሪነት አቀጣጣይነት በጎ ስራቸው ለተበላሸባቸው ትውልድና ለደከመች ቤተክርስቲያን ብርታትና ህይወት ሆነዋል። ከምንም ነገር በላይ ሰዎችን ወደ ክርስትና እምነት የሚያስገባው የመንፈስ ቅዱስ ስራና ፍሬ ነው። በትክክለኛው መንገድ የመንፈስ ቅዱስ ስራ በሰዎች ከተፈቀደለት በጎ ለውጦችን መልካም ፍሬን ያስከትላል። ጌታ ጠይቁ ይሰጣችኁማል ብሎ ከሁሉ በፊት ይኖረን ዘንድ መመሪያውን የሰጠን መንፈስ ቅዱስን እንድንቀበል ነው። (ሉቃስ 11:13)

<u>መንፈስ ቅዱስን አታሳዝኑ</u> መንፈስ

ቅዱስን ማሳዘን ብዙ የተለመደና የከፋው የሰዎች ችግር ሆኗል። መንፈስ ቅዱስ ባልታረመና ክፋት በተሞላው ልብና አንደበት በጣም ያዝናል። *"ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ አይውጣ። ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ።"* (ኤፌሶን 4:29)

መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን ከጌታ መለየትና ለዘላለም ሞት መዳረግ ስለሆነ ራሳችንን በመመርመር ዛሬውኑ ጌታን ይቅርታ እንጠይቅ። የበደልናቸውንም እንዲሁ በመጠየቅ በሰላም በደስታ ኑሯችንን እንቀጥል።

<u>የጥሞና ጊዜ በእግዚአብሔር ቃል</u>

<u>(በዳሬክ ፕሪንስ)</u>

ምድርና ሰማይ በውስጡ ያሉትም ሁሉ የተፈጠሩት በእግዚአብሔር ቃል ነው። ሰዎች የእግዚአብሔርን ሀሳብ የሚያገኙትና በረከቱን የሚቀበሉት ለሌሎችም የሚያደርሱት በቅዱስ ቃሉ ነው።

በጥሞና ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር በጸጥታ በመቆየት ከእግዚአብሔር ሁሉን መቀበል የሚቻለው በቅዱስ ቃሉ በሚደረግ ጥልቅ ጸሎት ነው።

የእግዚአብሔር ልብ ከሰዎች ልብ የተለየና የራቀ ሲሆን ይህን የሚያውቀው ጌታ እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ እርሱ የሚመልሰውም በቅዱስ ቃሉና በቅዱስ መንፈሱ ነው።

"ከአፌ የሚወጣ ቃል እንዲሁ ይሆናል የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም" (ኢሳይያስ 55:11)

የተበላሸውን የሰው ዘር ህይወት ከጠፋበት ወደ እግዚአብሔር የሚመለሰው በቅዱስ ቃሉ ስለሆነ ዘወትር በጥሞና ጊዜያችን በቅዱስ ቃሉ ራሳችን በመመርመር ወደ እግዚአብሔር መንገድ እንመለስ።

"እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት ቀርቦም ሳለ ጥሩት ክፉ ሰው መንገዱን በደለኛ ሀሳቡን ይተው እርሱ ይምረዋል፣ ይቅርታውም ብዙ ነው" (ኢሳያስ 55:6)

<u>የእግዚአብሔር ቃል የልብ ዓይኖቹን የከፈቱለት ሰው -ሰማዕቱ የማንቹሪያው ቻንግ</u>

ቻንግ ሼን ማንቹሪ ውስጥ በአሁኑ ታይዋን በታይፒካንግ መንደር ተወለደ። በ1878 የውጭ ሀገር ዶክተር ወደ ቻንግ ስፍራ ባይመጣ ኖሮ የቻንግ ታሪክ እንዲህ ሊጻፍ የማይቻል ገና በህፃንነቱ የሚሞት ነበር።

ገና በለጋነቱ በተላላፊ በሽታ የተያዘው ህፃን ቻንግ እንዲተርፍ በዚያ ስፍራ ዶክተር ክርስቲ በዚያ ክርስቲያን ሆስፒታል ቻንግን ከክፉ ደዌ ከሞት ሲያተርፍ ነፍሱን የሚያድን የሆስፒታሉ ወንጌላዊ ይህንን ህፃን በመንከባከብ በዚያ አሳድጎት ዶክተር ክርስቲ እንደመሰከረው ጌታን በልዩ ደስታ ሊቀበልና ሊያምን በቃ። በዚያ ከተማ ፍፁም ይተርፋል ብለው ያልጠበቁት ቻንግ ከዳነ በኋላ ለሚያገኛቸው ሁሉ በድንቅ ሁኔታ በመመስከር ብዙዎች ክርስቶስን ለማመን በቁ።

"እግዚአብሔር - የሚያቅትህ የለም" (ኤርሚያስ 32:17)

በሀገራችን ኢትዮጵያ በልዩ ልዩ የክርስቲያን የጤና ማእከሎች የስጋም የነፍስም ደህንነት ያገኙ ብዙዎች አሉ። ጌታ በዚህ መንገድ ስላሰማራቸው ልጆቹ የተመሰገነ ይሁን።

ለተጠራንበት ልዩ ስራ በሚገባ እንመላለስ

በዚህ የምጽአቱ የምስራች እትም ከቅዱስ ቃሉ ኃያልነትና ለዋጭነት ቀጥሎ በጣም ተፈላጊ የሆነውን የክርስቲያኖች ተገቢ አገልግሎትና ህይወትን የሚመለከቱ መልዕክቶች ይቀርባሉ።

በቅዱስ ቃሉ ሰዎች የክርስትና እምነትን በማግኘት ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ግንኙነታቸው ሲበረቱ የሚቀጥለው ደረጃ የእግዚአብሔር መንፈስ በአማኞቹ ላይ በመፍሰስ በጎ ህይወትን የተገባ ኑሮና ቅዱስ አገልግሎትን ይጎናጸፋሉ። *"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌም በይሁዳም ሁሉ በሰማሪያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"* (የሐዋሪያት ሥራ 1:8)

ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል ተነክተውና ተለውጠው በቅዱስ መንፈሱ ተሞልተው ለአገልግሎት ሲሰማሩ በጨለማው ዓለም ሰይጣን ያሰራቸውን ላለማስፈታት ትግል እንደሚያደርግና አማኞችም በዚህ ከሰይጣን ሰራዊት ጋር መንፈሳዊ ውጊያ እንዳለባቸው ቅዱሱ የጌታ ቃል ያሳስበናል። ክርስቲያኖች በዚህ የክርስትና ኑሯቸውና ስራቸው በከፍታ ያለው የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ የሚመራው መሆኑን ማወቅ ይገባቸዋል።

"የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው" (ኤፌሶን 1:18-19)

ኑሯችን በዚህ ኃጢያት ክፋት በሞላበት ዓለም ቢሆንም እኛ የምናገለግለው ዜግነታችን በከፍታ ያለው ንጉሳችን መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀመጠበት ልዩ ሰማያዊ ስፍራ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ክርስቲኖች በጌታ የተሰጠንን ከፍተኛ ሰማያዊ ስፍራ በመዘንጋት በዚህ በጠፊው ዓለም ለዘላለም እንደምንኖር ስንደራጅ ስንጨነቅ መታየቱ አሳዛኝ ነገር ነው። *"ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን ነገር ግን እግዚአብሔር በምህረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሳ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ህይወትን ሰጠን።"* (ኤፌሶን 2:5)

ለማይገባን ፍጥረቶቹ በክርስቶስ ተገቢ ስፍራ ያገኘን ህዝብ ነን። የእግዚአብሔር ልዩ ጥበብ በምድራዊ ተቋማት ሊገኝና ሊስፋፋ አይችልም። የእግዚአብሔር ልዩ ፍቅር፣ ሰላም፣ በረከትና ዘላለማዊ ህይወት የሚገኝበት ምድራዊ በሆነ ስፍራ በክርስቶስ የተመሰረተችው ቤተክርስቲያን ወይም የቅዱሳን ህብረት ወይም ማህበረ ምዕመናን ነው።

"ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ሰፍራ ውስጥ ላሉት አለቆች ስልጣናት ትታወቅ ዘንድ ይህም በክርስቶስ የተፈጸመ የዘላለም አሳብ ነበር።" (ኤፌሶን 3:10) ክርስቶስ ለእኛ ሁሉም ነው፤ አዳኛችን ነው። (ኤፌሶን 5:23) በደመ መስዋዕትነት ኃጢያታችንን አስወግዷል። (ኤፌሶን 1:7) መልካም መአዛ ያለው መስዋዕት ህይወቱን ለእኛ አቅርቧል። (ኤፌሶን 5:25)

በክርስቶስ ተስፋ ያልነበረን ሰዎች ዛሬ ባለተስፋዎች ነን። (ኤፌሶን 2:12) ክርስቶስ ራሱ ሰላማችን ነው። (ኤፌሶን 2:14) ያልታወቅን ምናምንቱ የነበርን በክርስቶስ የእግዚአብሔር መንግስት ዜጎች ሆነናል፤ ክርስቶስም የዚህ መንግስት መግቢያውና የማዕዘን ራስ ነው። (ኤፌሶን 2:18)

በክርስቶስ መሆን ምንኛ መታደል ነው! ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ህይወት የሆነልን የራሱን ህይወት ያለአንዳች ጥፋት በመስቀል ሞቱ በመክፈሉ ነው። *"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅየለሁ እኔ ግን አሁን ሕያው ሆኜ*

ሳልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል አሁንም በስጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለእኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት የምኖረው ነው።" (ገላትያ 2:20)

የክርስቶስ ኃይል በእኛ ይኖራል

እጅግ ብርቱ የሆነው የክርስቶስ ኃይል በእኛ ላይ ከእርሱ ጸጋና ምህረት የተነሳ በእምነት በእኛ ዘንድ ይኖራል። (ኤፌሶን 2:20)

በሌላ መልኩ መቃብርና ሞት ያላሸነፈው መታንን የሚያስነሳው የክርስቶስ ኃይል በእኛ ዘንድ አለ። ስለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ከምንጠይቀው በላይ አትርፎ ይህንን ኃይልና በረከት እንደሚሰጠን የጻፈልን። (ኤፌሶን 3:20)

በእነዚህ የተሰጉ ቃሎች መሰረት እኛ አማኞች በዚህ ምድር በሚኖረን ህይወትና ኑሮ ምንም መከራ ቢገጥመን ሳንረታ በብርታት የምንኖር ምንም ክፋትና ጥላቻ ቢበዛ እኛ የምህረትና የፍቅር ልብ ያለን ሆነን የዚህ ምድር ኑሯችንን ፈፅመን ወደዘላለሙ ቤታችን ለመሉ ክብር እንደርሳለን።

ጸጋው በእምነት ያድነናል

(በቻርለስ ስፐርጀን)

በክርስትና እምነት የደህንነትን ልዩ ትርጉም የሚሰጠው የእግዚአብሔር መገለጥ በሐዋሪያው ጳውሎስ የተጻፈ ቅዱስ ቃል የእግዚአብሔር ጸጋ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ሰዎች እንደሚድኑ የሚያስረዳ ነው። (ኤፌሶን 2:8)

እግዚአብሔር መሀሪ አምላክ በመሆኑ ኃጢያተኞች ልጆቹን በቅዱስ ቃሉና በመንፈስ ቅዱስ በማቅናት በኢየሱስ ክርስቶስ ባለ እምነት ከዘላለም ሞት ያተርፋል፤ ያድናል።

የእግዚአብሔር ጸጋ ምንድን ነው? ማንስ ጥልቀቱን ያውቀዋል? ለሚሉት ጥያቄዎች የእራሱ የእግዚአብሔር ቃሎች እንደሚከተለው ይመልሳሉ። *"እግዚአብሔር ፍቅር ነው"* (ዮሐንስ 4:8) የእግዚአብሔር ልዩና ገደብ የሌለው ፍቅር ዘላለማዊ ነው። (መዝሙር 135:1)

"ምህረቱ ዘላለማዊ ነው"

"እስመላለምህረቱ"

"ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምህረት የተነሳ ነው" (ሰቆቃወ ኤርሚያስ 3:22)

በዚህ የእግዚአብሐር ፍቅር እኛ ኃጢያተኛ የሆን የሰው ልጆች ምህረት አገኘን። የእኛ እምነት ብቻውን ሳይሆን ከእግዚአብሔር የሆነ ጸጋ ሲወርድ ምህረት የማይገባን በእምነት ምህረት አገኘን። *"የእምነታችን ጀማሪና ፈፃሚ ክርስቶስ ነው"* ዕብራውያን 12:2

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በሚኖር በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ የሚፈጠር በቃሉ ውስጥ ያለፈው እምነት የእግዚአብሔርን ምህረት አስገኘልን።

በእምነት መጽደቅ የሞራልና የስነምግባር ብቃት ሳይሆን የክርስቶስ ብቃት ያስገኘልን ነው። ሰላማችን የሆነው ክርስቶስ ለእኛ ምግባር የለሾች ሞራል ለጠፋብን ብቃት ሰጥቶ ጨዋዎች አደረገን።

ይህን የተቀዳጀንበት በክርስቶስ ቃል የሚገኘው እምነታችን እንዳይጠፋ ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል። በትንሽ የሰናፍጭ ቅንጣት እምነት ብዙ ተዓምራቶችን መስራት እንደምንችል ጌታ ራሱ ያስተማረንና ቃል የገባልን ያረጋግጣል። (ማቴዎስ 17:20)

የእግዚአብሔር ኃይል የሚገለጠው ሰዎች ደካማነታቸውን አውቃው ወደ እርሱ ሲጮሁና እርሱ ጌታ ብቻ መታመኛቸው ሲሆን ነው። (ሐዋሪያት ስራ ምዕራፍ 2)

የትንሳኤው ኃይል

"ገበደላችን መታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ህይወት ሰጠን" (ኤፌሶን 2:5)

አንድ ሰው ትንሳኤ የሚያገኘው ካለመኖር ወደ መኖር ከሞት ወደ ህይወት ለዘላለም ሲሻገር ነው። የወንጌል ትልቅ መልዕክት በራሳችን አንዳች በጎ ነገር ማሰብና መወሰን የማንችል ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ብቻ በጎ ማሰብና መፈጸምን በእኛ እንደሚሰራ ይገልጽልናል። *"ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሰራ እግዚአብሔር ነውና"* (ፊልጵስዮስ 2:13)

የክርስቶስ ህይወት በሰው ጥረትና ባህርይ ትጋት የሚቀየር ሳይሆን በመለኮታዊ እግዚአብሔር ቃልና ኃይል የሚለወጥ ነው። የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተገለጠው ወደ ሰዎች ሲዘልቅ መታን የነበሩ ህያዋን፣ ክፉዎች የነበሩ ደጎች፣ አመንዝራ የነበሩ ጭምቶች፣ የተቅበዘበዙ የተረጋጉ ይሆናሉ።

ይህ ሰማያዊ ለውጥና አመለካከት በክርስቲያኖች ህይወት የሚገለጸው በክርስቶስ ቃልና መንፈስ በትንሳኤው ኃይል ስፍራችን/ሀገራችን ምድራዊ ሳይሆን በሰማይ ሲሆን ነው። ያም መንፈሳዊ ህይወት ነው። *"እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሳችሁ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለምና።"* (ቆላስያስ 3:1)

በክርስቶስ ሙሉ እምነት ያለው ሰው ለዚህ ዓለም ጉዳዮች ማለትም ለዓለማዊ ክፉ ስራዎች የሞተ ነው። የሞተ ሰው ደግሞ የሞተበትን ነገር አይሰራም፣ አይደግምም። *"ምታችኋልና"* (ቆላስያስ 3:2)

ለዓለም ለስጋና ሰይጣን ስራ ያልሞቱ ሰዎች ለቤተሰብ ለቤተክርስቲያንና ለሀገር ክፉ ስር ይሆናሉ። በሌላ በኩል ለዓለምና ለስጋ የሞቱ ሰዎች በድል አድራጊነት በክርስቶስ ህይወትን በማግኘት አሮጌውን ሰው አስወገደው፤ በአዲሱ ሰው በቅድስና ይኖራሉ። (ቆላስያስ 3:9 ፣ ኤፌሶን 4:22)

ይህ የክርስቶስን ትንሳኤ የተቀበለ ህይወት በግልፅ የሚታይ የቅድስና የደግነት የህይወት ባህርይ ያለው ነው።

የዚህ ዓይነቱ ተግባራዊ የክርስቲያን ኑሮ የሚታየው አንድ ሰው ለዓለማዊ ነገሮች ለሰይጣን ስራዎችና ለስጋዊ ፍላጎቶቹ በመሞት ከክርስቶስ ጋር በትንሳኤ የተሞላ ህይወት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲቀዳጅ ነው። ከመጀመሪያውም ሰዎች በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የክርስትና የትንሳኤ ህይወት ይኖሩ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሚሰጣቸው ሁሉ የድል ህይወትን እንዲኖሩም ያው መንፈስ ያግዛቸዋል። በዚህ ምድር ኑሯቸው በክርስቶስ በእውነት ያመኑትን ማንም ሊከሳቸው እንደማይችል ሆኖም ግን ክርስቶስ ብቻ ፈራጅ ሊሆን ከሙታ መነሳቱን ቃሉ ያረጋግጣል። (የሮሜ መልዕክት 8:34)

የክርስቶስ ትንሳኤ ኃይል ክርስቲያኖችን ህይወታቸውን ሁሉ በእምነት ሲኖሩ የሚቀድስ የሚያበረታና ለሌሎች በወንጌል እንዲደርሱ የሚያስችል ብርቱ ጉልበት ያለው ነው።

ሐዋሪያው ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ አሁን እኔ አልኖርም እንዳለው ክርስቲያኖች በዚህ ምድር ህይወታቸው ለዓለም ነገሮች ለስጋ ፍላጎቶችና ለሰይጣን ስራዎች የተሰቀሉ የሞቱ መሆናቸውን መረዳት ይኖርባቸዋል። (ገላትያ 2:2)

በክርስቶስ ትንሳኤ የፈውስ በረከትም አለ። በትንሳኤው ዕለት ማለዳ ከመቃብር ፈንቅሎ የተነሳው ጌታ ከሁሉ በላይ ስልጣን ያለውና ያንን ስልጣን በስሙ ላመኑ ሁሉ ያቀዳጀ ነው። (ሐዋሪያት 1:8)

የክርስቶስ የትንሳኤው ኃይል በክርስትና ህይወት ለሚገጥመን ችግርና ጥያቄ ሁሉ መፍትሄ የሚሰጠን ነው። ይህም ማለት ሁሉም ችግርና ፈተና ይወገዳል በማለት የምኞት መስቀል የለሽ ወንጌል ሳይሆን ማንኛውንም መከራ ችግር ማስወገድ ባይቻል የሚያስችል ኃይል እና እምነት የሚሰጥ ነው። ከክርስቶስ ፍቅር አንዳች መከራ አይለየንም። (ሮሜ 8:35)

ለመንፈሳዊ ውጊያ የፀሎት ጥሪ

የሐዋሪያው ጳውሎስ መልዕክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች የሚጀምረው ክርስቲያኖች በሰማያዊ ስፍራ በክርስቶስ እግዚአብሔር የሰጣቸውን በረከትና ስልጣን በማሳየት ነው። ወደ ምዕራፍ ስድስት ስንደርስ ግን ጉዳዩ ክርስቲያኖች የሚኖራቸውን መንፈሳዊ ውጊያ ወደማስረዳት ይሸጋገራል።

በኤፌሶን 6:10 ላይ ክርስቲያኖች ከጠላት ሰይጣን ጋር የሚኖረን ፍልሚያ ይብራራል። ይህ ለክርስቲያኖች በክርስትና ህይወታቸው የማይቀርላቸው የትግል አይነት ነው። ክርስቲያኖች የሚኖራቸው ውጊያና መንፈሳዊ ጦርነት በመንፈስ ቅዱስ ብቻ የሚከናወን ነው። ይህም ውጊያ ክፉ ከተባለው የርኩስ መንፈስ አለቃና ሰራዊት ጋር ነው። (1 ዮሐንስ 5:19)

ለዚህም ብርቱ መንፈሳዊ ውጊያ ክርስቲያኖች ተገቢውን መንፈሳዊ ትጥቅ መያዝ እንደሚገባቸው ቅዱስ ቃሉ ያስረዳል። (ኤፌሶን 6:11)

የክርስትና ተዋጊ ጦር ለመንፈሳዊ ውጊያ የሚይዘው አንዳች ምድራዊ ወይም ስጋዊ መሳሪያ የለውም። የክርስቲያን መንፈሳዊ ጦርና ትጥቁ ጌታ ኢየሱስ ዋና አዝማቹ የተጠቀመበት ቅዱስ ቃሉ ብቻ ነው። (ማቴዎስ 4:7)

የመንፈሳዊ ውጊያ ትልቁ ወይም ብቸኛው ነዳጅ ወይም ኃይል ደግሞ በጸሎት የሚገኝ የመንፈስ ቅዱስ በኃይል ነው። (ኤፌሶን 6:8)

የምድር ጦርነቶች ሁሉ ማቆሚያ ጊዜ ሲኖራቸው እኛ ክርስቲያኖች በዚህ ምድር ኑሯችን ከሰይጣን ጋር የሚኖረን ጦርነት የማያቋርጥ ነው። ስለዚህም በቃሉ መፀለይና በጸሎት ሳናቋርጥ ኃይሉን ከጌታ መጠየቅ የግድ ነው።

"ሳታቋርጡ ጸልዩ" (1 ተሰሎንቄ 5:17) ሰይጣን እጅግ የሚጣላውና የሚዋጋው ሰዓት የጸሎት ጊዜን ነው። በጸሎት ጊዜያችን ልዩ ልዩ መሰናክሎችና ጉዳዮችን ሰይጣን ወደ ክርስቲያኖች እንደሚልክ ተረድተን በጽኑ ልንቃወመውና የጸሎት ጊዜያች በምንም እንዳይቀይር መትጋት ይኖርብናል።

የጸሎት ህብረታችን ከቅዱሳን ጋር በልብ አንድነት በመሆኑ ለልባችን የከበደብንን በይቅርታ ሳንገላለጽ ብንጸልይ መልስ ከጌታ አናገኝም። (1 ቆሮንቶስ 12:25 ፣ መዝሙረ ዳዊት 65:18) *"በልቤስ በደልን አይቼ ብሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር"*

የጸሎት ህብረት አገልጋዮች በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። በእነዚህ ሰዎች ለማንኛውም የወንጌል ስራና ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ብርቱ ጸሎት ሊካሄድ ያስፈልጋል። በጸሎት ህብረቶች ስንፍና፣ በጸሎት ስም አሉባልታንና የሌሎችን ምስጢሮች እንዳናሰራጭ ለዚህ የተገቡ ጥንቃቃ ታማኝ ሰዎችን መመደብ ይገባናል።

ከእያንዳንዱ የሰዎችን ልብ የሚያረካ እግዚአብሔርን የሚያስከብር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያሳይ መንፈስ ቅዱስን የሚያሰርፅ ብርቱ ጉብኝት ጀርባ ብርቱ ጸሎት ይኖራል። *"በአንድ ልብ አብረው ሆነው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ።"* (ሐዋሪያት 2:2)

የፀሎት ህብረት አገልጋዮች የሚጸልዩባቸው ጉዳዮች የበለጠ የሰዎችን መዳን ያስቀደመ ሊሆን ይገባዋል። ጉዳዩ በቅደም ተከተል የሰዎችን ከገሀነም ከሰይጣን እስራት ማስፈታት ጀምሮ ወደ ምድራዊ አስፈላጊ ጉዳዮች ምግብ መጠለያና ጤናን ለሰዎች መስጠትን ሊያካትት ይችላል። ብዙውን ጊዜ ጸሎት በስጋዊ ፍላጎት ላይ ብቻ ካተኮረ መሳት ስለሚመጣ ጸሎት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የእግዚአብሔር ማዳን ለጠፉ በሚደርሰበት ይሞላና ይቀድም ዘንድ ይገባል።

የጸሎት ተጋዳይ ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙ ጊዜ የሚያስቀድመው የጸሎት ርዕስ ወይም ጥያቄው ላልዳኑት ወንጌልን ለማድረስ የጌታ ጥበብና ኃይል እንዲመጣለት በማሳሰብ ነበር። *"የወንጌልን ሚስጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለእኔ ለምኑ።"* (ኤፌሶን 6:19)

ሐዋሪያው ጳውሎስ የክርስቶስን ወንጌል በልዩ ትጋት ስለሚያሰራጭ ሰይጣንም ባለ በሌለ ኃይሉ ይዋጋው ስለነበር የጌታን ልዩ ኃይል

ለማግኘት የጸሎት ርዕሶችን ያቀርብ ነበር። ለዚህም "ለእኔ ደግሞ ጸልዩ" ብሏል።

የተዋጣለት ጸሎት ለማካሄድ የጸሎቱ ጉልበት ሰጭ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን መሞላት በጣም ተፈላጊ ጉዳይ ነው። (ኤፌሶን 5:18) ይህ ቅዱስ መንፈስ በየጊዜው እየፈሰሰብን የበለጠ ሊያሰራጭ እንዲችል መንፈስ ቅዱስን ከማሳዘን እንቆጠብ፤ እንጠንቀቅ። (ኤፌሶን 4:30) በቅዱስ መንፈሱ በመሞላት በጸሎት በክርስቶስ ድል ለማድረግ ሁልጊዜ በቃሉ በጽድቅ ጦር እንታጠቅ። (ኤፌሶን 6:13)

የአመፃን መሪ ሰይጣንን ስለመፋለም

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት በሉቃስ 10:17 ላይ የአመፃው የክፋቱ መሪ ሰይጣን ከጌታ የተነሳ እንደተንበረከከላቸው በደስታ ሲናገሩ ይታያል። *"አጋንንት በስምህ ተገዝቶልናል"*

ሆኖም ግን በዚያ ዘመን ኃያል ሆኖ ሰዎችን የሚያሰቃየው የሚያስረው ሰይጣን በአንድ በኩል ሁሉን ቻይ ጌታ በሌላ በኩል ሆነው ደቀመዛሙርት በመሃል ግራ ተጋብተው የሚገኙበት ሁኔታ በዛሬው ዘመናችንም የቅዱሳን ህብረት ኃያል ሆኖ ሲሰራ በሌላ በኩል የዓለም ፖለቲካና ውጥረት ሲነግስ ከቅዱስ ቃሉና ከፀሎት ርቀን ስንጠወልግ በጭንቀት በተስፋ መቁረጥ እንዳንገኝ ሁሌም ድል አድራጊ የሆነውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንታመንበት።

ደቀ መዛሙርቱ ከብዙ አገልግሎትና ቆይታ በኋላ ወደ ጌታ ሲመጡ ከማረጉ በፊት የሰጣቸው ስልጣን ይህንን በክፉ ሰይጣን በዓለምና በደካማ ስጋቸው ላይ የበላይና አሸናፊ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታና ኃላፊነት *"ስልጣን ሰጠኋችሁ"* በማለት ይገልጸዋል። (ማቴዎስ 28:18)

የሚገርመው ግን ይህን ያህል ስልጣን ለልጆቹ (ቤተክርስቲያን) ከሰጠ ለምን ይህ ሁሉ ምስቅልቅልና ፍርኃት በክርስቲያኖች ዘንድ ይደርሳል የሚል ነው።

ለዚህ መልሱ አንድና አንድ ነው። ያም የሰይጣን "ሐሰት" ነው። ሰይጣን ከጌታ ጋር የሚወዳደር አንዳችም ጉልበት የሌለው ነው። የተሸነፈ ጠላት ነው። ክርስቲያኖች ስልጣን ተቀብለናል፤ ተሰጥቶናል።

ሰይጣን በፍርኃት ተሸናፊ ሊያደርገን ሲሞክር በክርስቶስ ያገኘናቸውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎቻችን እንመስክር፤ እንፈውስ፤ እንተንብይ፤ እንጸልይ፤ እንመላለስ። (ገላትያ 5:23)

በዚህ ዘመን ክርስቲያኖች በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ጌታ በመንፈስ ቅዱስ እፍ ብሎ ያሰማራቸውን ደቀመዛሙርት ያህል ስልጣንና ጸጋው ያለን ሆነናል። ምክንያቱም ያው ክርስቶስ ትናንትም ዛሬም እስከዘላለም ድረስ ያው ነውና። (ዕብራዊያን 13:8)

"በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ።" (ኤፌሶን 1:3)

ሐዋሪው ጳውሎስ የተገለጸለት እኛም የተገባን ቦታ ስፍራችንን ማወቅና መጠቀም ነው። ያም በሰማያዊ ስፍራ በጌታ ቀኝ ነው። (ኤፌሶን 1:19)

ልጆቻችንን በጌታ ቃል እናሳድጋቸው

"ልጅህን በእግዚአብሔር ቃል ምራው ባደገም ጊዜ ከዚያ ፈቀቅ አይልም።" (ምሳሌ 22:6) *"ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሳጽ አሳድጓቸው።"* (ኤፌሶን 6:4)

ልጆች ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ አዳማዊ ኃጢያት ያለባቸው በቅዱስ ቃሉና በእግዚአብሔር ጸጋ አዳማዊ ክፉ ተፈጥሯቸው ሊወገድ የሚገባው መሆኑን ቃሉ ያረጋግጣል። *"እነሆ በዓመፃ ተፀነስሁ፣ እናቴም በኃጢያት ወለደችኝ"* (መዝሙር 50:5) ልጆች የመጀመሪያ ሰባኪያቸው ወላጆቻቸው እናትና አባት የቀሩትም የቤተሰብ አባላትና ጎረቤቶች ናቸው።

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው በሞኝነት ባለማስተዋል ልጆች ለክፉ ኑሮና መከራ የበለጠም ደግሞ ለሰይጣንና ለተከታዮቹ ሊዳረጉ ስለሚችሉ ይህ ግድ የሚለን በቅዱስ ቃሉ የዘላለም የቅድስና በጎ ህይወትን እንስተምራቸው። *"ሸንፍና በህፃን ልብ ታሰርሶልል ጆሮህን አዘንብለህ የጠቢባንን ቃላት ሰማ ልብህንም ወደ እውነት አድርግ።"* (ምሳሌ 22:15)

ልባችን እንደመሬት የተዘራበትን ሁሉ የሚያበቅል ስለሆነ የልጆቻችንን የራሳችንንም ልብ ከክፉ ዘር በመጠበቅ መልካም ዘር እንዝራበት።

ልጆች በጥበብ ይሞሉና መልካም የቅድስና ህይወት ይኖራቸው ዘንድ ወላጆችና ኃላፊነቱ ያለባቸው ሁሉ ግድ ሊላቸው ጥበብን ሊያስተምሯቸው ክፋትንም በመግለጥ እንዲርቁት ያስተምሯቸው ዘንድ ያስፈልጋል።

ልጆች ከሚነገራቸው ይልቅ በተግባር የሚያዩትን ስለሚለማመዱ ወላጆች በተግባር ፍቅርን ሰላምን ትህትናን ራስን መግዛትንና ደግነትን በህይወት ምስክርነት አሳዩአቸው።

ፍቅር የመሳካትና የማደግ ትልቅ መሳሪያ ስለሆነ ልጆች/ህጻናት ሁሉ በተቻለ መጠን ፍቅርን እንስጣቸው፤ እንግለጽላቸው።

ሳኦልን የመሰለ ለልጁ ለዮናታን ክፉ የሚመክር አባት መልካምነትን አያስተላልፍም። (1 ሳሙኤል 20:30)

ግብዝነትን ሌብነትን ማስመሰልና ማናቸውም ክፉ ስራ ልጆቻችን ከእኛ እንዳይማሩ መጠንቀቅ አለብን፤ በሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ዙሪያ በትውልድ የሚታይ ብዙ ክፋት ከወላጆች የሚማሩት የሚወርሱት ነውና። *"አባቶች ሆይ ልባቸው እንዳይዝል ልጆቻችሁን አታበሳጩዋቸው።"* (ቆላስያስ 3:21)

ከሁሉ በላይ ለልጆች የሚተላለፍ ትልቅ ቅርስ ጥበብ ሲሆን የሰማይ ጥበብ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ ከሁሉ የበለጠ ጥበብ ነው።

ይህንን ልዩና ዘላለማዊ ጥበብ ለልጆቻችን የሚገለጸውና በልባቸው የሚያስቀረው መንፈስ ቅዱስ ብቻ በመሆኑ ከልጆቻችን ጋር አብሮ በመጸለይ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ እንዲሞሉ መትጋት ይኖርብናል።

የልጆቻችሁ ነገር በእውነት ግደ የሚላችሁ ከሆነ ልጆቻችሁን ከክፉ የሚጠብቅና ለዘላለም የሚያኖር በምድራዊም በሰማያዊም ጥበብ የሚሞላውን የእግዚአብሔር ቃል ስጧቸው። ለልጆቻችን ጤና፣ ምግብ፣ ትምህርትና ቅርስ የምናስበውን ያህል ይህን ሁሉ በረከት የሚያፈልቀውን ለዘላለም የሚያፀናቸውን ቅዱስ ቃሉን ለገዛ ልጆቻችን ከማካፈል ችላ አንበል። በልጆቻችን ፊት ሀቀኝነታችንን ስናጠፋ ይቅርታ መጠየቅን ኃጢአት ምን እንደሆነ በማስተማር ንስኃ በመግባት ማሳየትን እናለማምዳቸው።

የበደል የጥፋተኝነት ስሜት በሰው ህይወት የሚከሰት መሆኑን እና በደልና ጸጸት በቅዱስ ቃሉና በእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ የሚወገድ መሆኑን በቃልም በተግባርም እናስተምራቸው። አዕምሯችን በተሞላው ነገር የሚመራና የሚሄድ በመሆኑ ለራሳችንም ለልጆቻችንም የየጊዜውን ቃል እንመላው።

በእግዚአብሔር ቃል የተሞላ አዕምሮና ቤተሰብ በፈተናና በመከራ የሚጸና ለሌሎችም በረከቱ የሚተርፍ ይሆናል። ትልቁ ስጦታ መጽሐፍ ቅዱስን ልጆቻችን የሚረዱትን ትርጉም እናበርክትላቸው።

የጸሎት ልማድ ለልጆች እናስተምራቸው። ልዩ ልዩ የቤተሰብ ልማዶችና ባህሎች ያሉትን ያህል የፀሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታ ባህል በቤታችን በማድረግ ልጆቻችንን የጸሎትና የቃሉ ሰዎች እናድርጋቸው።

ጸሎት ክርስቲያናችን የሚያንቀሳቅስ የህይወት ሞተር በመሆኑ ኑሯችን እቅዳችን በሙሉ በጸሎት የተሞላ እንዲሆን ልጆቻችን ይረዱልን።

የእግዚአብሔርን ቃል ችላ የሚል ትልቁን የጥበብና የህይወት ባርኮት እንደሚያጣ ይታወቅ። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉልን በሙሉ ለማነፅና ለበጎ ምክር መሆኑን በመረዳት ለልጆቻችን ይህን ልዩ ዘላለማዊ ስጦታ አንንፈጋቸው። *"የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ስራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትን መጽሐፍ ሁሉ ልብን ለማቅናት ይጠቅማል።"* (2 ጢሞቲዎስ 3:16)

ዓለም አቀፍ የጸሎት ርዕሶችና ዘገባዎች

ከኢትዮጵያ

የምጽአቱ የምስራች የእንኒለዘኛውን እትም ላለፉት 30 ዓመታት በመጠቀም ላይ እገኛለሁ። ይህን አገልግሎት ለምትሰጡን ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ። የጋዜጣው መልዕክት ልቤን በመንካት የክርስትና ህይወቴ አድጎበታል። ባለሁበት ማህበረ ምዕመናን በየወሩ በሚደርሰኝ አገልግሎት እየሰጠሁበት ነው።

ከኬንያ

እግዚአብሔርን ለየምጽአቱ የምስራች የተባረከ አገልግሎት ማመስገን እፈልጋለሁ። ይህንን የምጽፈው በብዙ ደስታና ሀሴት ተሞልቼ ነው። ገና በወጣትነቴ ከ19 ዓመቴ ጀምሮ መልዕክቶቹ በህይወቴ ያስቀሩልኝን በረከት መታነጽ አልረሳም። ሁሉን ቻይ አምላክ ይህንን ጋዜጣችሁን የበለጠ ይባርከው፤ ያስፋው።

ከእንግሊዝ (ብሪታንያ)

የምጽአቱ የምስራችን ከአስር ዓመታት በላይ በመከታተል ላይ ነኝ። በክርስትና ህይወቴ በመልካም ጉዞ ላይ እድገኝ ጋዜጣችሁ ረድቶኛል። ከሀሰት ትምህርቶች እንድጠበቅና ሰዎችንም በጤናማ ትምህርት ይፀኑ ዘንድ ለመምከር ረድቶኛል። የጸሎት ህይወትን ጭምር ላስተማረኝ ጋዜጣችሁ የከበረ ምስጋናዬን ተቀበሉኝ።

ከኤርትራ

በየምጽአቱ የምስራች ጽሁፎች የማነኛቸውን በረከቶች ለመዘርዘር ቃላቶች ያጥሩኛል። የከፋውን ኑሮና የክርስትና ስደት ባለሁበት ሀገር በመቋቋም በእምነቱ እጸና ዘንድ ይህ ጋዜጣ በጣም ረድቶኛል።

ከጋና

እግዚአብሔር ስለዚህ ጋዜጣ አገልግሎታችሁ ይባርካችሁ። በቅዱስ ቃሉ መሰረት በምትልኩልን መልዕክት የዘላለም ቅርስን አግኝተናል።

ከካናዳ

የመጽአቱ የምስራችን ብቃት ያላቸው መንፈሳዊ ጽሁፎች ስለምትልኩልኝ ላመሰግን እወዳለሁ። እግዚአብሔር አምላክ ለዘላለም ይባርካችሁ።

ከሴሪላንካ

ስለምትልኩልኝ የምጽአቱ የምስራች ጋዜጣ በጣም አመሰግናለሁ። በመንፈሳዊ ህይወቴና በጸሎት እንዳድግ ጋዜጣው ብዙ ረድቶኛል።

ከፍሎሪዳ

የምጽአቱ የምስራች ስለሚላክልኝና በጥሞና ጊዜ ስለምጠቀምበት መንፈሳዊ ጽሁፋችሁ አመሰግናለሁ። የክርስቶስ ቤተሰብን የሚያንጽና የመንፈስ ቅዱስን እሳት የሚልክ ጋዜጣ ነው።

መልዕክት ከተርጓሚውና አስተባባሪው

አደፍርስ (ኤዲ) ሀብቴ መካሻ

ይህ የምጽአቱ የምስራች የትርጉም ስራዎችን እንድጀምር ለመጀመሪያ ጊዜ የእንግሊዘኛውን ኮፒ ከ28 ዓመታት በፊት የሰጠኝ በዚያን ወቅት የአዲስ አበባ መካነ ኢየሱ ሽማግሌ የነበረው ወዳጀ አስፋው በንቲን ክልብ ለማመስገን እወዳለሁ። በመቀጠልም ትርጉመን ሳቀርብ የተባረኩትና በብዙ እጥፍ አሜን ያነቃቁኝ የአዲስ አበባ መካነ ኢየሱስ ወጣቶችን ሳላመሰግን አላልፍም።

ትርጉመን በእጅና በታይፕ በመተየብ አብረውኝ በመጀመሪያው ዘመናት የተጉትን የንግድ ስራ ኮሌጅ ባልደረቦቼን ቆንጂት ወ/ማሪያም መስፍን፣ ፀጋዬ ሰፋኒት አክሊሉ

ዲዛይኑን ከሰራልን ባለቤቲ አንተነህ አያሌው ጋር ሁልጊዜ አመሰግናለሁ::

ሀትመቱ በቀጠለ ጊዜ የረዱኝን የራሴን ቤተሰቦችና ዘመዶች ውድ ባለቤቱን ፋንታዬ ግርማን ልጆቼን ቀዳማዊት ስምረትን የባለቤቱ እህቶችን አልማዝ ዓለማየሁና የወቅቱ ተጠሪዬ አልማዝ አሳየን ከነቤተሰባቸው ላመሰግን እወዳለሁ:: ከሁሉ በላይ በዚህ በስነጽሁፍ አገልግሎት እንድተጋለት መሸቱን በልቤ ላስቀመጠው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፍቅሩ የወደደኝ እግዚአብሔር አብና ኃይሉን የሚያፈስልኝን መንፈስ ቅዱስን አከብራለሁ::

በአማርኛ ትርጉሙ ይጀመር ዘንድ መጀመሪያ ጥያቄውን ለአሜሪካ አሳታሚ ያስታወቁት የቅድስት ማሪያም አዲስ አበባ ቤተክርስቲያን የሰንበት ተማሪዎችም ብድራት አለብኝ::

በዚህ ትርጉም ስራ ለሰርጭቱ ለተለያዩ አገልግሎቶቹ በገንዘብ በጸሎትና በምክር ለረዱኝ ወገኖች ሁሉ ምስጋና ይድረስ:: በአብያተ ክርስቲያናት ደረጃ በይፋ የረዱኝ የአማኑኤል ሀብረት ቤተክርስቲያን የተባረኩ ይሁኑ::

ማሳሰቢያ

አሁንም ይህን አገልግሎት ለሚጠይቁን ሁሉ መላክ እንድንችል በጸሎትና በገንዘብ ድጋፋችሁ እንዲደረግልን በጌታ ፍቅር እጠይቃለሁ::

- ተጠሪ አልማዝ አሳየ ስልክ
  0912120402 የፖ.ሣ.ቁ
  8986 አዲስ አበባ

ልዩ የጸሎት ርእስና ማሳሰቢያ

ይህንን እትም ትርጉም በምናዘጋጅበት ወቅት በአሜሪካ ያለው ዋናው አሳታሚ በሀገራችን ላለፉት 28 ዓመታት የነበሩትን ችግሮች ስደቶችና ጉዳቶች በጸሎት በምልጃ ሲያቀርቡ ቆይተው በዚህ ወቅት ዶ/ር አብይና ባልደረቦቻቸውን በመጠቀም ጌታ ስላመጣው በጎ ለውጥ በዓለም ዙሪያ በእንግሊዘኛ ምስጋና ቀርቧል::

ሆኖም ግን አመስግነን ሳንጠግብ በቡራዩ አካባቢና አስቀድሞም በሶማሊያ ክልል በደቡብ በሀዋሳ በወሊቂጤ በህዝባችን ላይ የደረሰው ጭፍጨፋ ከቶም በባህላችን የማይጠበቅ ግድያና የሴቶችና ህጻናት መደፈር ልባችንን እጅግ ነክቶታል::

ሆኖም ግን የበጎ ነገር ሁሉ ምንጭ የሆነው እግዚአብሔር ይህንን ክፋት ሁሉ ያስወገደና የሚያስወግድም ነውና ሳንታክት እንድንጸልይ አንዳች የክፋት፣ የዘረኝነት የዓመፅ ስራ ተባባሪ፣ ተነጋሪና አስተላላፊ እንዳንሆን ሁሉንም እንመክራለን:: በዚህ ህትመት በተዘገበው መሰረት ያኔ በሀገር ቤት ተቃዋሚዎች የሰጡንን ዛቻ ማስጠንቀቂያ ሁሉ በይቅርታ አልፈናል:: በህይወታችን እንዳየነው ያሳደዱንን ያስፈራሩን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሳውል (ጳውሎስ) ያገኛቸው ዘንድ አሁንም ጸሎታች ይቀጥል::

መላው ህዝባችን ሁሉንም ዘርና ሁሉንም ፖለቲከኞች ወገን አድርጎ የሚቀበል ዶክተር አብይ አህመድን ጌታ ስለሰጠን ስሙን በትልቅ ደስታ ከፍ እናደርጋለን:: ለሀገራችን ህዝብ ለመሪዎቻችን ለፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና ለዚህ ሁሉ ሃላፊነት ላለባት ለተኛችው ለደከመችው ለተከፋፈለች የኢትዮጵያ አንዲት ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ እንድትነቃ እንድትዘጋጅ እንድትጠራ በያም በፀሎት የገባን ሁሉ ለድል ህይወት እንድንዋደቅ፤ እንጠይቃለን::

የምጽአቱ የምስራች ወንጌል መነቃቃት
አገልግሎት

ሄራልድ ኢንተርናሽናል ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ ጋዜጣ

ዶ/ር አብይ አህመድን አደነቀ

ከሃምሳ ዓመታት በላይ በህትመት የቆየው ወደ ሰላሳ የሚጠጉ አማርኛ ጭምር በትርጉም ስራዎች በዓለም ላይ የሁሉንም ክርስቲያን ክፍሎችን መነቃቃትና ጉዳት በመዘገብ የታወቀው በፊት በኒውተን ካንሳስ በአሁኑ ወቅት ሲ.ልቪ. ኢንዲያና መቀመጫውን ያደረገ የአሜሪካ ትልቁ ጋዜጣ በደ/ር አብይ የሚካሄደውን የኢትዮጵያ ለውጥ ሃደት አደነቀ። ብዙ ታዋቂ የዓለማውያን ጋዜጦች ዶ/ር አብይን በማድነቅ ላይ ሲሆኑ ከክርስቲያን ዓለም አቀፍ ጋዜጦች ይህ የመጀመሪያ መሆኑ ለሀገራችን ክርስቲያኖች ተጨማሪ ደስታ ነው። ጋዜጣው ያለምንም የሐይማኖትና የዘር ልዩነት የሚያደርጉት በጎ ጅምር በማድነቅና በማመስገን ተጨማሪ ጥበብ ፈጣሪ ይሰጣቸው ዘንድ ተከታዮቹን የፀሎት ትብብር ጠይቋል። ሄራልድ ኢንተርናሽናል "የምጽአቱ የምስራች" በሚል ርዕስ ላለፉት ሃያ ስድስት ዓመታት በአማርኛ ሲሰራጭ የቆየ ሲሆን በዓለም ዙሪያ ከ5000 በላይ ተከታዮች በአማርኛ ኮፒ ይደርሳቸዋል። የጋዜጣው ትርጉም የጀመረው በአዲስ አበባ ቅድስተ ማሪያም ቤተክርስቲያን የሰንበት ተማሪዎች ባሳሰቡት የቀደመ ጥያቄ መሰረት በሀገራችን የልጆችና የማህበራዊ ጉዳዮች ትርጉም ባለሙያ አደፍርስ(ኤዲ) ሀብቴ መካሻ ታዋቂ የልጆች መጽሐፍ "ከራተኛው ድመት" ተርጓሚ ውክልናውን በበጎ ፈቃድ በሀገር ቤት በመጀመር በአሜሪካም ለመቀጠል ችሏል። ጋዜጣው በተጀመረባቸው ዓመታት በወያኔ ህውኃት በሽግግር መንግስት ተቀባይነት ተሰጥቶት የድሮ መኮንኖች ክበብ ቢሮውን አድርጎ ሲንቀሳቀስ በኢትዮጵያ መ.ስ.ለ.ሞች ዘንድ ተቀባይነት የሌለውን አክራሪነት የጀመረ (IFLO) የዛቻ ማስጠንቀቂያ ልኮለት ነበር። ይህ አሸባሪ ድርጅት በሀረር የክርስቲያኖች ግድያ እጁ ያለበት ሲሆን የአክቲቪስት መስፍን ፈይሳን አባት ቤተክርስቲያን ውስጥ ማረዳቸውን አክቲቪስት መስፍን መስክሯል። IFLOን ያደራጀውና መጠቀሚያ ያደረገው ህውኃት ከተጠቀመበት በኋላ መሪዎቹን በማሳደድና በማሰር ለማስወገድ ቢጥርም በአካባቢው በነበሩ ተመሳሳይ ድረጅቶች ውስጥ መግባታቸው ሲታወቅ በአሁኑ ወቅት ህልውናው በይፋ የማይታወቅ ሆኗል። ላለፉት ሃያስድስት ዓመታት ሄራልድ ኢንተርናሽናልም ሆነ የአማርኛው ትርጉም ስለኢትዮጵያ ስቃይ ለዓለም በማሳወቅ የተጉ ሲሆኑ ብዙ ጊዜ በምልጃ በሱባኤ የሚጠቅሷት ሀገራችን ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በምስጋና ርዕስ በዓለም ዙሪያ ላሉ በመቶ ሺዎች ለሚጠጉ ተከታታዮቻቸው ማሳወቃቸው ደስታ ሊሰጠንና ሊመሰገኑም ይገባል።

ከየምጽአቱ የምስራች

የትዝታ ማህደር

ይድረስ ለምጽአቱ የምስራች መፅሔት ጸሀፊዎች እኔ የድሮዋ ወይንሸት የአሁኗ ፋጡማ እባላለሁኝ። አሁን እኔ ያለሁት በIFLO ታፍኜ ሐይማኖቴን ቀይሬ ሴቶች ማህበር ዋና ሀላፊ ሆኜአለሁ። እስላም ለመሆኔ ዋና ምክንያት በበግ ግልገል አላህ የሚባል ፅሁፍ በመታየቱ ነው።

ስለዚህ አንተና ወረቀቱን የሚያትሙትን ድርጅቶች ይህ ያልሆነ አይነት ወረቀት መበተናችሁን ብታቆሙ ይሻላል። ያለበለዚያ የ IFLO ሽምቅ ተዋጊዎች ለድርጅታችሁ የሚያሰጉ ስለሆነ በአስቸኳይ ለድርጅት ማለትም ለ IFLO መልሱን ላኩልኝ።

በሉ አላህ ሱብሃናሁ
ወታለን
የ IFLO ማህተም የሚነበብ